# ኢትዮሚዲያ
# ትችት
# የውሸት ቀን ጥበብ
(ትርጉም መላኩ ፀጋዬ መኮንን)

አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ምስጋናና እውቅና መስጠት ተገቢ ነው።መለስና ጀሌዎቹም እንደዚህ የውሸት ቀን ጥበብ ሙያተኞች በመሆናቸው ሙሉ ምስጋና ሊቸራቸው ይፈልጋሉ። ልክ ቀለስላሳው ወንጀለኛ ሲያዝ ሁሉንም ይክዳል ሌቦ "ይህን ፈፅመህል" ከዚያ ተፈፅሞ ይሆናል ወይም እንዴ! ምን አልባት አንዱ አድርጎት ይሆኖል፣ አንዱ የእኔን የእጅ አሻራ ሰርቆ ይሆናል። በእኔ ለማስመሰል (ለማመካኘት)፣ ክህዳት፣ ክህዳት፣ክህዳት፣

ቀስ በቀስ ኢትዮጵያን እየከባባት ያለውን ርሀብ አስመልክቶ መለስና ግብረበሎቹ ይኸነው መልሳቸው የምን ርሃብ? የምን ድርቅ? ድርቁ ከክልል ወደ ክልል እየተዛመተ ሕዝቡን በማደረስ ላይ ስለአለው ድርቅ ከጥቂት ቀናት በፊት የወያኔ አንቀልባ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር" አዲሱ ለገሠ ቅሬታውን ሲገልጥ በኢትዮጵያ የደረሰውን የምግብ እጥረት የተጋነነና ከራሳቸው የውስጥ ፍላጎት ጋር የተሰላ ነው።" ብኋል "በመለስና በድርጅቱ የማዛባት ሚኒስቴር (ማስታወቂያ) ሁሉም ድርቅ የሚባለው የውጭ መገናኛ ብዙሀንና የሰብአዊ እርዳታ ለጋሾች ትንበያና መላምት ነው" የሚያሳዝነውና የሙያ ስነምግባር የሌላቸው አንዳንድ የመገናኛ ብዙሀን የምግብ እህል ዋጋ መናር በኢትዮጵያ ብቻ የተከሰተ አይነት እንደሆነ መቅረቡ ነው። እዚህ ላይ በአሁኑ ወቅት የሚታየው የአለማቀፍ የዋጋ መናር፣ በአሁኑ ወቅት የነዳጅ ዋጋ መጨመር በታዳጊ ሀገራት ሁሉ የዋጋ ከፍ ማለትን አስከትኋል። የአንዳንድ መገናኛ ብዙሀን ዘገባ በጣም የተጋነነ እና ከእዉነት የራቀ ነው። ይላል ይህ የማዛባት ሚኒስቴር የተምታታ መግልጫ ፣

የመለስ ድርጅት ማሳረጊያው በኢትዮጵያ ድርቅ የሚባል የለም። በሚሊዩን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ግን የምግብ ዋጋዉ በመጥፎ ሁኔታ በመጨመሩ የተነሳ የመግዛት አቅምየላቻውም
ይላናል ልብበሉ መላስ በጣም ጮሌ የሆነ የማታለያ ዘመቻ ያካሂዳል። በኢትዮጵያ የምግብ ዋጋ መናር አለማቀፍን የእቃ አቅርቦት ገበያን ማመካኘት የኢትዮጵያ ግፅታ እንዲበላሽ የውጭ መገናኛ ብዙሃንና የእርዳታ

ለጋሽ ድርጅቶች እያደረጉ መሆኑን ማማረር እየከፋ የመጣውን ረሃብ ከሕዝብ ክትትል ለማውጣት፣ በአደባባይ ከሕዝብ የራቀዉን የምግብ ገበታ ባዶነት መዋሸት የድርቁን አስከፊ ገጽታ መሸፈን በየጊዜዉ አሽናፊነትን ማወጁ ሀገሪቱ ባለፈዉ አምስት አመት በተከታታይ በእጥፍ ምጣኔ ሀብት ማድጉን”

እዉነታዉ ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ እየተራብ ነው። በየቀኑ በሽዎች የሚቆጠሩ በረሀብ እየሞቱ ነው። ይህ አጠያያቂ አይደለም አሉ ማርጋሪት አካየር የካልፎርኒያው የአለማቀፍ የህክምና ቡድን ቃል አቀባይ በቅርቡ እንደገለጡት “በቂ ምግብ የለም፣ የምግብ እጥረት አለ። ሁሉም እየተራቡ ነዉ። ይህ ነዉ እውነታዉን በኢትዮጵያ የአለም የምግብ ድርጅት ዳሬክተር ጅያ ሻበር ተመሳሳይ ጉጽታ ያለው መልክታቸው ላይ 14 ሚሊዮን ሕዝብ በስድስት ደቡባዊ አፍሪካ ሀገራት የምግብ እርዳታ ያስፈልገዋል ካሉ በኃላ፣በኢትዮጵያ በአንድ ሀገር ብቻ 14 ሚሊዩን ቁጥር ያለዉ ሕዝብ የምግብ እርዳታ ይሻል ሲሉ የችግሩን ስር መስደድ ተናግረዋል።

ከዚህ ላይ ለምንድን ነው ማርጋሪት አኳየር፣ ጆርጅ ሸበር፣ቢቢሲ፣ ሴኤንኤን፣ አልጃዚራ የመሳሰሉት ስለኢትዮጵያ ድርቅ የሚዋሹትና ድርቁን በማጋነን የሚጠቀሙት ምንድን ነው?

## የቸነፈር እውነታዎች

ካለፉት 30 አመታት በላይ ኢትዮጵያ በአለማቀፍ ደረጃ የድርቅና የርሃብ ማስታወቂያ እመቤት ሆና ቀርባለች። አስቡት እሰኪ በቅርበትም ተመልከቱ፣ አጥንታቸው የወጣ ህጻናት እና የተራቡ ወላጆቻቸው በፀሃይ የደረቀ የልጆቻቸው ገላን ሲያኩ፣ በአለም ዙሪያ ባለው ሕብረተሰብ ምስሉ ጥሎት ያለፈውን ትዝታ መፋቅ አልተቻለም። በ1966 ያልታወቀው/ ድብቁ ርሃብ በጆናታን ዲቢልቢል እና በሌሎች የውጭ ሀገር ጋዜጠኖችና በአንዳንድ የአለማቀፍ እርዳታ ሰጭ ድርጅቶች አማካኝነት የመጽሃፍ ቅዱሱ የጥፋት ቃል ጋር በማነጻጸር በስሜት የሀገሪቱ ክፍል የደረሰውን ድርቅ ከተላለፈ በኃላ አመጸኛ ወታደሮች አፄ ኃይለስላሴን ከስልጣን አወረዱ።

ልክ መለስ በአሁት ወቅት እንደሚያደርገው ሁሉ ኃይለስላሴ ድርቅና ረሃብ መኖሩን ካዱ፣ አስተባበሉ፣ ለመሸፋፈን ሞከሩ፣ የረሃቡ ዜና አለምን

ሲያስደነግጥ ኃይለስላሴ የውጭን መገናኛ የኢትዮጵያን ገጽታ ለማኮሰስ ሲሉ ችግሩን ማጋነናቸውን በማማረር ተናገሩ።

በ1977 ከ10 አመት የሶሻሊዝም ሙከራ በኃላ በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ በረሃብ አለቀ። መንግስቱም በበኩሉ ለመቆጣጠር ሞከረ በዝናብ እጦትና በድርቅም አሳበበ። ነገር ግን የአፍራሹ የሶሻሊዝም መርህ (ፖሊሲ) መሆኑን ግን መቀበል አልፈለገም። ችግሩን ለመፍታትና ብሎም ለወደፊቱ የሚያመጣውን ችግር ያላገናዘበ የግዳጅ እንደገና ማቆቆም(መንደር ምስረታ) በመቶ ሺህ ዎች የሚቆጠር ሕዝብ ከስሜን ወደለሙ የደቡብ የሀገሪቱ ክልል አዛወረ። አሁን መለስ እንደሚያደርገው አይነት መንግሥቱ የአለም አቀፍ የምግብ እርዳታ ቤቱ ድረስ በገፍ እንዲመጣለት እጁን አጣጥፎ ጠበቀ። መለስ ዛሬ በኢትዮጵያ ያለው የድርቅ ችግር፣ ያምው ካለ? የችግሩ ምክንያት የዝናብ እጥረትና ድርቅ ነው (ነገር ግን የእርሱ አገዛዝ የምጣኔ ሀብት መመሪያ አይደለም ይኸው የጤፍ ምርት እንዲጨምር ከማድረግ ይልቅ የአበባ ተክልን ቅድሚያ መስጠት። አሁን ታዲያ ግዙፍ የምዕራቡ አለም በገፍ የምግብ እርዳታ በሩ ድረስ እንዲልኩና ኢትዮጵያን እንዲታደጉ ይጠብቃል። ልክ ኃይለስላሴ 1965 የአለማቀፍ የነዳጅ ችግር የተነሳ የነዳጅ ዋጋ መናር የምግብ ግዝ ዋጋ ከፍ ማለት ከውጭ ሀገር የሚገቡ እቃዎች ዋጋ ማደግ እና ድርቅ ላይ እንዳመካኙት ሁሉ መለስም ዛሬ የዘይት ዋጋን በ2000 ዓ.ም. መጨመር ያሳብባል።

## የመለስ የውሸት ቀን ጥበብ

መለስና ግብረበሎቹ የውሸትን ጥበብ በትክክል ወደ ከፍተኛ እርከን በሚከተሉት ምክንያቶች አሸጋግረውታል።

*እውነትን በመካድ፡* መካድ የማይቻለውንና ፊት ለፊት የሚታይን ያፈጠጠ እውነት ይክዳሉ። ለምሳሌ "ረሃብ ኢትዮጵያ ውስጥ የለም የውጭ ሀገር የእርዳታ ድርጅቶችና የመገናኛ ብዙሀን በሙሉ የፈጠሩት ችግር ነው። ሁሉም የተጋነና ከእውነት የራቀ ነው ይላሉ።

*ሀላፊነትን መካድ፡* "እራሱ ድርቅ መኖሩን ይክዳሉ ለምሳሌ" ድረቅ የለም ነገር ግን ልክ እንደማይለቅና እንደሚጣበቅ ነገር አለ። በመጀመሪያም ሆነ በመጠረሻ ሀላፊነቱ የእግዜአብሄር (የፈጣሪ) ነው። በመልካም ፈቃድ

የሚለግሰውን ዝናብ አቆመ፣ ዝናብ እንዲዘንብ አላደረገም፤ በመሆኑም አዝመራ የለም፣ ይህ ማለት ድርቅ ነው። እግዚአብሄር ከፈጠረው ሚስጢራዊ ችግር ጋር የነዳጅ ዋጋ መናርና የስግብግብ የአለም አቀፍ ገበያ ፣የምግብ ዋጋን ጨመረበት። የመጀመሪያና የመጨረሻ የሌለውና የማያቆመው የምዕራባዊያን ጥፋት ነው። እንደዚሁም ባለፉት 30 አመታት ያደረጉትን የምግብ እርዳታ የመስጠት ሀላፊነታቸውን ዛሬም መቀጠል አለባቸው። ስለዚህ ምንም  ልናደርግ የምንችለው ነገር የለም። ወደ ራሳችን ስራ ጉዳይ አሁን እንቀጥል፣ አበባ እንትከልና ምጣኔ ሀብታችን በእጥፍ ቁጥር እናሳድግ ።

**ተፅዕኖን መካድ፣** በሀገሪቱ ምንም አይነት ድርቅ የለም። አንዳንድ አካባቢ የእህል አቅርቦት እጥረት አለ ለምሳሌ " ከኦሮሚያና ከሱማሌ ክልሎች ውጭ ሁሉ ነገር በገፍ እንደልብ ይገኛል። ሕዝቡ የመግዛት የገንዘቡ አቅሙ ካለው በቀሪዎቹ የሀገሪቱ ክፍሉች ምግብ ተትረፍርፏል"

## የቅድመ ማስጠንቀቂያን መካድ

በጣም ሥራ በስቶብን ነበር "የሀገሪቱን ምጣኔ ሀብት በእጥፍ በማስዳግ" ተጠምደን ሥራ  በዝቶብን ነበር ። እንደዚሁም የአበባ ምርትን በማሳደግ በጣም ተደምደን ነበር፣ ድርቅ ስለመኖሩ አልሰማንም፣ ለምሳሌ "ባለፉት አምስት አመታት የመጣኔ ሀብቱ በተከታታይ በእጥፍ ባደገበት ሀገር ረሀብ ሊኖር ይችላል ብሎ መገምት የማይታሰብ ጉዳይ ነው፣ የመስሪያ ቤቶችን መዋቅርን መዘርጋት፣ ፎቆችን የመገንባትና የውሀ ገንዳዎችንና ታላላቅ በአለም ደረጃቸውን የጠበቁ ሆቴሎችን ማሰራት፣ አበባ ወደውጭ በመላክ የፈረንሳይ ወይን እና ሻምፓኝ ስናስመጣ፣ በጣም ስራ በዝቶብን ነበር። በአጭሩ በገጠሩ ረሃብ ማገርሸቱን አላወቅነም፣ በቃ  እናዝናለን"

**ተደጋጋሚ ክህደት፡** ምን አልባት ድርቅ ካለ አሁን ተከስተ ለምሳሌ "ይህ ድርቅ በድጋሚ እንደሚመለስ አላወቅንም፣ ቅድመ ማስጠንቀቂያ አልነበረም፣ ይህ እውነተኛ ረሃብ ይመጣል ብሎ ተጠንቅቆ የጠበቀ የለም፣ ለማንኛውም ትልቅ ነገር አይደለም፣ እኛ በእጥፍ የኢኮኖሚ እድገት ላይ ነን፣ ልክ እንደሌሎቹ ነገሮች ሁሉ ይህ ድርቅም አሁን ይወገዳል፣ ዝምብሎ እኮነው፣ በየአስር አመቱ እየቆጠረ የሚመጣው"፤

**የክህደት ክህደት፡** በድርቅ ጉዳይ ላይ እንድንስራ ግዴታ የለብንም። ለዚያውም ርሀብ ካለ ነው! ለምሳሌ ድርቁ ሁሌ የራሱን ጊዜ ይወስዳል፣ ሁሉም ድርቅ በኢትዮጵያ ለአስርተ አመታት ነበር። ይህ የመጀመሪያው አይደለም። በድርቁ ምንም የተፈጠረ ነገር የለም በ1965 እና በ1977 ከነበረው የሕዝብ ቁጥር አሁን ጨምራል በመሆኑም ድርቅ በሕዝብ ቁጥር እድገት ላይ የሚያመጣው ለውጥ የለም። ሁሉም ድርቅ በራሱ ጊዜ ጨርሶ ያልፉል። ተፈጥሮአዊ ነው ምንም ማድረግ አያስፈልገንም።

**ክህደትን በማመን መካድ፡** ሁሉ የድርቅ ጉዳይ የሚበን ነገር ነው “ይጋነናል” ለምሳሌ “እውነት ነው በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕዝቦች በምግብ እጥረት አደጋ ላይ ወድቀዋል። ነገር ግን አንዳንዶች በኢትዮጵያ ድርቅ ብለው ከሚገልፁት የባሰው የምግብ ዋስትና ማጣታቸው ነው። እነዚህ በአለም መገናኛ ብዙሃን የሚታዩት አጥንታቸው ያገጠጠው ታዳጊ ልጆች ተመጣጣኝ የሆነ አልሚ ምግብ የጎደላቸው ናቸው። ነገር ግን በምንም መለኪያ የድርቅ ሰለባዎች አይደሉም። ወላጆቻቸው በበርካታ ጊዜ የምግብ እጥረት የገጠማቸው እንጂ፣ በድርቅ የተነሳ አይደለም። ትልቁ አስከፊ ሁኔታ የኢትዮጵያ የምግብ ሁኔታ በብዛት የምግብ እጥረት መከሰቱ ነው። ይህም ከድርቅ ጋር ተመሳሳይ አይደለም ”

## ምን ነው ኢትዮጵያ በድግግሞሽ በድርቅ የምትደናቀፈው?

ኃይለስላሴ በድርቅ ምክንያት ከስልጣን ሲወርዱ። ሕዝቡ ለምን ድርቁን ለመከላከል እርምጃ አልወሰዱም ብሎ ጠየቀ? መንግስቱ የ10ኛ አመቱን የሶሻሊዝም መንግስት ሲያከብር በመቶ ሺህዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በድርቅ ይረግፉ ነበር። ሕዝቡ አሁንም ጠየቀ፣ አንድ ነገር ለምን ለመከላከል የሚያስችል እርምጃ አልወሰደም? አሁንም ተመሳሳይ ጥያቄ ለመለስ መቅረብ አለበት። የሚሊኒየሙን ክብረበአል በታላቁ ቤተመንግስት በፌስታ ሲያከብር ለምን ድርቁን ለመከላከል እርምጃ አልወሰደም? ለጥያቄው መልስ በጣም ቀላል ነው። መለስ ጉዳዬ አይደለም። ከጠቅላላ ሕዝቡ ከፊሉን ድርቅ ጠርጎ ቢወስደው ምንም ደንታ አይሰጠውም። ምን አልባት ጥቂት የአዞ እንባ ጠብ ይለው ይሆን? የእርሱ ዋና ትኩረት እራሱንና ግብረበሎቹን ከስልጣን የሚያቆይበትንና ኢትዮጵያ የእነርሱ መጫዎቻ ገበታ ሆና እንድትቀጥል ማድረግ ነው።

ይህ ፍፁም እውነት ነው። አሁን በጣም አስጊ ስለሆነው ወቅታዊ ድርቅ ይዘት ብቻ ሳይሆን ጠለቅ ብለን ጉዳዩን እንመልከተው፤

የማይታበለው እውነት ድርቅ በኢትዮጵያ ውስጥ የተፈጥሮ አደጋ አይደለም። አወ፣ በአንዳንድ የአካባቢዎች ጉዳዮን ሊያባብሱ የሚችሉ የተፈጥሮ የአየር ፀባይ ክስተቶች አሉ። ነገር ግን ድሮም አሁንም መከላከል ይቻላል። ነገር ግን ችግሮቹ የሰው ሰራሽ ችግሮች ናቸው። በመሆኑም ከባድ ጥያቄዎችን ለ17 አመታት በመንበሩ ላይ ፊጢጥ ብለው ድግስ የሚውጡትን መለስና ግብረበሎቹን መጠየቅ ግዴታችን ነው።

- እውን መለስ በ1965/66 እና1985/1986 ዓ.ም ከተከሰቱት ቸነፈሮች በመነሳት 1999/2000 ዓ.ም. ድርቅን ለመቋቋም ትምህርት ወስዷል?

- ለምንድን ነው በመለስ አገዛዝ የድርቅ መከላከል ከፍተኛውን ፖሊሲ/ትኩረት ያልተሰጠውም/የማይሰጠው?

- በማንኛው ሀገራት ለምግብ ዋስትና መረጋገጥ የግል የመሬት ይዞታ መፍትሄ መሆኑ እየተነገረ፣ ለምን መለስ የመሬት ይዞታን ወደ ግል ለማዛወር እንደ ቋጥኝ ድንጋይ ተገትሮ ቆመ?
- በሚለዮን የሚቆጠር ሕዝብ በቸነፈር እየረገፈ ለምንድን ነው መለስ በርካታ ሚሊዮን ዶላር ያለማቋረጥ ለሱማሊያ የሚያፈሰው?

- ሚሊዮን በሚሊዮን የሚቆጠር ረሃብተኛ በሀገሪቱ እያለ፣ በተቃራኒው የኢትዮጵያን አመታዊ በጀት ግማሹ ለወታደራዊ ወጭ ለምን ተመደበ?

- የጤፍና የስንዴ ምርትን በማሳደግ ረሃብተኛውን ኢትዮጵያዊ ከመመገብ ይልቅ የአበባ ንግድ ወደ አውሮፓ ለመሸጥ ቅድሚያ ለምን አስፈለገ?

- መለስ ለምን ከፍተኛ የወሊድ ቁጥር ያለባቸው ሀገራት እንደሚያደርጉት ሁሉ ብሔራዊ የቤተሰብ ምጣኔ የአወላለድን እቅድ ለምን በተግባር ላይ አያውልም? ለምንስ መለስ በአለማቀፍ ምግብ እርዳታና ላይ ጥገኛ ሆነ? ለምን እነርሱ እንዲታደጉን ይፈልጋል?

- ለምን ኢትዮጵያ በ1999 ዓ.ም. የምዝበራ አለማቀፋዊ ማጣራት ከ179 ሀገራት 138ኛ ወጣች?

## ድርቅን መጠቀሚያ ማድረግ

በድርቅ አጥንታቸው የሰለለ፣ መተንፈስ ተስኖቸው ጫን ጫን የሚያቃስቱ፣ የመጨረሻ እስትንፋስ ላይ ሆነው ውጭ ነብስ ግቢ ነብስ የሚታገሉ ልጆች እና እናቶቻቸው የደረቁ ገላቸውን የሚመለከቱበት ብቻ አልሆነም። አሁን የወታደራዊና የፓለቲካ መጠቀሚያ መሳሪያ ሆኗል። መለስ ዛሬ አመፅ ያካሂዳሉ በሚባሉ "በደቡብና ደቡባዊ ምስራቅ አካባቢዎች ልክ መንግስቱ እንዳደረገው" የአመፀኛ አካባቢዎች" በሰሜን በነበረ ጊዜ እንደሆነው ሁሉ የምግብ እርዳታ እንዳይደርሳቸው እያደረገ ነው።ይህ መለስ ከመንግስቱ የተማረው ስልት ነው። ድርቅ አንድን ተቃዋሚ ለማጥቃት እቅድና ስልት ይወጣለታል። ችግር ፈጣሪ የተባለውን አካባቢ የሕዝቡን ቁጥር እንዲቀንስ በማድረግ ያገለግላል። ነዋሪዎቹ ይሰደዳሉ። በመሃሉ ሽማቂዎችን ለይቶ ለመምታት ይጠቀሙበታል። ልክ ማኦ ሴቱግ እንደተናገረው "ሽማቂዎች ልክ እንደ አሳ ናቸው ሕዝቡ አሳዎቹ የሚዋኙበት ውሃ ነው" ድርቅን ስትጠቀምበት ታዲያ ልክ ውሃውን ከሃይቁ ስበህ ማውጣት ማለት ነው። ውሃ የለም አሳ የለም" ስለዚህ ችግር አከተመ ማለት ነው።

ድርቅ ማንኛውንም የተደራጀ ተቃዋሚ ለማጥፋት የፓለቲካ መሳሪያ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል። ለምሳሌ ወደ ከተማ የሚደረገውን የእህል ሽመታ በመቆጣጠር አገዛዙ የከተማውን ነዋሪ እግሩ ስር እንዲወድቅ ማድረግና ማንኛውንም ተቃዋሚ ለማጥፋት ይገለገልበታል። ከዚህም ሌላ ለችግር አትራፊዎች/የችግር ጊዜ ነጋዴዎች/ ድርቅ እራሱ በጣም ጠቃሚ ነው። የአገዛዙ ተግባሪ ነጋዴዎችና የእርሻ ሰብል አይነት ድርጅት ከገበሬው በገፍና በርካሽ የገዙትን እህል እነርሱ በወቅቱ ከገበያው ዋጋ ባነሰ በመሸጥ አነስተኛ እና በችርቻሮ ንግድ የተሰማሩትን ከገበያ ያስወጡአቸዋል።

እነዚህ ተባባሪ ነጋዴዎች የግብርናውን ውጤት ሙሉ በሙሉ የመግዛቱን፣ የማከማቸቱንና የመሸጡን ሲቆጣጠሩ፣ በተለይ እህልን በድርቅ ዘመን መሸጥ ትርፍ በማከማቸት በኩል ምን ያህል ውጤታማ እንደሆነ መገመት አያዳግትም። በድርቅ አትራፊዎች ዘንድ የምጣኔ ሀብተቸውን ገቢ

በመመልከት ድርቅን ለማስወገድና ለመቆጣጠር የሚሰጡት የፖሊሲ ትኩረት ዝቅተኛ ነው። ይህ የአረጀው የአቅርቦትና የፍላጎት ቁርኝት አዙሪት ቀመር ነው። የምግብ ፍላጐት ከፍተኛ የገበያ አቅርቦቱ ዝቅተኛ ስለሚሆን እንደፈለጉ ይቸረችሩታል እንደዚሁም ሙሉ በሙሉ አለማቀፍ እርዳታውን መቆጣጠር ለመለስና ግብረበሎቹ "ሀብት በሀብት ላይ ማከማቻ ዘዴ ነው"

## በኢትዮጵያ የድርቅ ድግግሞሽ እውነተኛው ምክንያት

ዋናው የወቅቱ የድርቅ መንስኤ የመለስ ዜናዊ የተዛባ የምጣኔ ሀብት እቅድ የአፈፃፀም ስልቱ ነው። ይህ ድምዳሜ የአብዛኛዎቹ የምጣኔ ሀብት አሠራር ላይ ልምድ ያካበቱትየምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች ሀሳብ ነው። ልክ አማርቲያ ሴን የአለማቀፍ ኖቤል ተሸላሚና ሎሬት እውቁ የልማት ምጣኔ ሀብት እድገት ባለሙያ እንደተገነዘቡት "በተግባር ላይ በዋለ የብዙሁን ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ውስጥ ምንም አይነት ረሃብ የሚባል የለም"

በኢትዮጵያ ውስጥ ድርቅና ሌሎች የአየር ጠባያት ለድርቅ መባባስ እንደ ተጨማሪ ጉዳዮች ናቸው። ነገር ግን እነዚህን ተፅዕኖ በቀላሉ በተግባር ሊውል በሚችል መመሪያ፣ እቅድን በማሻሻል፣ የተሻለ የማስተባበሪያ ስልት በመቀየስና የብዙሃን ዴሞክራሲያዊ የፓርቲ ስርዓት በመፍጠር መቆጣጠር ይቻላል። ነገር ግን በአንድ ፓርቲ የፈላጭ ቆራጭ አስራር፣የተራበን ሕዝብ በመመገብ ፈንታ በተለይም የአበባ ቁጥቋጦንና የቡና ውጭ መላክን፣ በቱሪዝም፣ በቪላ ግንባታ፣ አላስፈላጊ በሆነ የመስሪያ ቤቶች መዋቅር ግንባታ ላይ ማተኮር የድርቁ ችግር በተገቢው መንገድ መፍትሄ አያገኝም። በምንም መልኩ ሰው ሰራሽ የዋጋ ዝቅተኝነትን በመፍጠርና የአገዛዙ ተባባሪ አቀባይ ነጋዴዎችን በትርፍ በትርፍ በማድረግና በመቀጠልም ከዚህ ግባ የማይባል ማበረታቻ መሳይ ነገር ለገበሬው በመቸር ገበሬዎች ለአገዛዙ ድምፅ እንዲሰጡ ማዳበሪያ እንደ መደለያ በሚሰጥበት ኢትዮጵያ፣ ረሃብን ለማስወገድ እንደማይቻል መታወቅ አለበት። በምግብ ምርት የአለም ባንክና አለማቀፍ የገንዘብ ተቋም በሚሰጡት ምክር ከተማመን እና መመሪያውን በእነርሱ መሰረት ካደረገና የግል ይዞታን ሚና ውሳኝነት በኮሰሰ ስርአት፣ የምግብ ምርት አድጎ ከረሃብ እንወጣለን ማለት ዘበት ነው። ድርቅ ለመታደራዊና ለፖለቲካ ጠቃሚታ ከዋለ በምንም ረገድ ሊወገድ አይችልም።መሬት ወደ ግል ይዞታ ካልተዛወረ በስተቀር ረሃብ ኢትዮጵያ ውስጥ በዘላቂነት ይኖራል።

# ኢትዮጵያ እጇን ወደ እግዜብሔር ትዘረጋልች!

እውነቱን እንጋፈጥ ባለፉት 30 አመታት ኢትዮጵያ በተደጋጋሚ ድርቅ እንድትመታ በግዴለሾች፣ በቸልተኖች፣ በምን ጉዳይ ባዮች፣ ትኩት በማይሰጡ፣ ሀላፊነት በማይሰማቸው፣ በአላማ ቢሶች እና በዋጋ ቢስ መንግስታት እንድትጠቃ ተገዳላች። የምግብን ዋስትና ለማረጋገጥ መፍትሄአቸው የመዋቅር ችግር፣ የልመና እጅን ወደ ምዕራባዊያን መዘርጋት። ባለፊት 30 አመታት የምግራቡ አለም ለተጠየቀው እርዳታ በትህትና በጥሩ ስሜት በመልካም ቸርነት በመረዳት በችሮታና በፍቅር ተባበረ። ዛሬ የምዕራቡ ልገሳ የመጨረሻው ደረጃ ላይ ደረሰ።በተለመደው አሰራር ለመጀመሪያ ጊዜ ምዕራቡ ኢትዮጵያን የመታደግ የሞራል ግዴታ የለበትም። የኢትዮጵያ "መንግስት" እጁን አጣጥፎ በተቀመጠበት ሁኔታ ወይም አንድ ነገር ሰራም ከተባለ ለልመና እጅን መዘርጋት ነው።

ምዕራቡ አለም በኢትዮጵያ ድርቅ የሞራል ስም ማጥፋት ይኖርብኛል ብሎ ከማይቀጠልበት ደረጃ ደርሶአል። ለዚህም ነው ይህ ወቅት የተለየ የሚሆነው ቦብ ጊልደፍስ ኢትዮጵያን ለመታደግ ዛሬ አይቆምም፣ ምንም የሕይወት ማዳን እርዳታ የለም። የሚካኤል ጃክስን "እኛ አለም ነን" የሚለው ዘፈን የለም። አሁን እጃችን ወደ ምዕራብ ኃያል አለም የምንዘረጋበት ሁኔታ የለም። በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ እጆቿን ከፍ ወደ አለው ኃይል መዘርጋት አለባት። ብቸኛው ኢትዮጵያን የሚያድነው ኃይል ኢትዮጵያም የምትድነው ያለምንም ጥርጣሬ በመጽሐፍ ቅድሱ በመዝሙሩ 68.31 በተፃፈው "ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዜብሄር ትዘረጋለች" እናም እጆቿን ይዞ ብሶቱን ያብሳል፣ ከመቀመቅ ያወጣታል፣ከድህነትና ሰቆቃ፣ ከጭቆና ማነቆ ይስወራታል። በዚህ ጊዜ የኢትዮጵያ ልጆች እጃቸውን ሳይሆን በግድ እጅ ለእጅ ተጨባብጠው እርስ በእራስ መረዳዳት የልገሳ እጃቸውን መዘርጋት በመላ አለም የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን በየቀኑ በሞት አፋፍ ላይ የሚገኙትን ወገኖቻችን መታደግ ያለብን ጊዜ አሁን ነው።